EthioLion

ፓኖራማ ቁጥር 93

የትዝብት አድማስ

ሐምሌ 21 2002 ዓ ም

## የጀግኖች ሐውልት ሲነቀል
## የባዕድ አምልኮ ጣዖት ሲተከል

በ19ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ወራሪ ሠራዊት ኢትዮጵያን ለመያዝ በቀይ ባኅር ተንሳፎ በመምጣት ምፅዋ ላይ ሰፈረ። የምፅዋን ወደብ የማዘዣ ጣቢያው አድርጎ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቆ ለመግባት ዝግጅቱን አጠናቀቀ ። የመጀመሪያውን ጦር እንቅስቃሴ በማድረግ ከምፅዋ 19 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘውን ዶጎአሌ በመባል የምትታወቀውን ቦታ ያዘ ። ይህን የወረራ ጥቃት ለመመከት በራስ አሉላ የጦር መሪነት የተንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ጦር የኢጣሊያንን ወራሪ ኃይል በ1879 ዓም ለወሬ ነጋሪ እንኳን አንድም ሳያስቀር ሁሉንም ደመሰሰ ። በጊዜው የተመዘገበው ዜና መዋዕል፥ በዚህ ውጊያ ላይ አምስት መቶ የኢጣሊያ ወታደሮች እንደተገደሉ ገልጾታል ። የዚህ ጦርነት ዉጤት መርዶ መላውን የኢጣሊያ ሕዝብ ስለ አስደነገጠውና ስለአስቆጣው በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ተቃውሞውን በማሰማቱ ደጎአሌ ላይ ለተገደሉት የኢጣሊያ ወታደሮች ቤተሰብ ማፅናኛ እንዲሆን ታስቦ በሮማ ከተማ የአምስት መቶዎች አደባባይ ( PIASSA CINQUECENTO) የሚባል ሐውልት የኢጣሊያ መንግሥት እንዲሰራ ተገደደ ። ይህ ሐውልት አሁንም ኢጣሊያኖች እንደስማዕታት መታሰቢያ አድርገው ያከብሩታል ።ኢትዮጵያ ሀገራችንም የዶጎአሊ ጀግኖቿን ክብርና ውለታ ለማስታወስ ስትል በጦሩ መሪ በራስ አሉላ ስም በቦታው ሐውልት ሰርታ እንደነበር ሁሉም የሚያውቀው ነው ። ያ ሐውልት ዛሬ ፈርሷል። መቸ ፥ ማን እና ለምን እንደፈረሰ መዘርዘር የለብንም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህና አድርጎ ያውቀዋልና !

ኢትዮጵያ የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ ብቻ ያላት ሀገር ናት ብለው የተነሱት ፀረ ኢትየጵያ ቡድኖች ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ እንዳልነበረች አድርጎ ታሪኳን ለማጥፋት በሚያደርጉት ጥረት ፥ ሐውልቶችን ፥ ቅርሳቅርሶችን ፥ የታሪክ መዛግብትን ፥ መፃህፍትን፥ ወዘተ ማጥፋታቸው የሚጠበቅ ስለሆነ የሚያስደንቅ ሆኖ አናገኘውም ። ወያኔ ከመነሻው ጀምሮ ለዚህ ዓላማና ግብ የቆመ በመሆኑም የጥፋት ዘመቻውን ቢቀጥል ከቶ ማንንም ዜጋ

ሊያስገርም አልቻለም ፡፡ ምናልባት ተተኪውን ትውልድና መጭውንም ታሪክ ጭምር ሊያስገርመውና ሊያስደንቀው የሚችል ነገር ቢኖር፥ የጀግኖችን ታሪክ እያፈረሱ የባዕድ አማልክት ጣዖት መገንባቱ ነው፡፡የወያኔው የፖለቲካ ካድሬ ሆኖ በማገልገል የወያኔን ተልዕኮ በማስፈፀም ላይ ያለው አባ ገብረመድህን ጳውሎስ በቅርቡ ምስለ-ሳጥናዔል ሐውልቱን አሰርቶ ወገኖቹን ሰብስቦ ማስመረቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቀት ትዝብት ተመልክቷል ፡፡ ይህ ድርጊት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተክርስቲያን ቀኖና መርሃ ግብር የሚፃረርና የሚያዋርድ መሆኑን ቢረዳም፥ የኢትዮጵያ ምዕመን ከቶውንም አይገርመውም፡፡ ምክንያቱም ይህ ሀሳዊ መሲህ ፥ የወያኔ ካድሬ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን የማይወክል በመሆኑ ፥ የሞራል ሥልጣንም ይሁን የሚያስከብር ሰብዕና ስለ ሌለውም ጭምር ነው ፡፡ ይህ ከፍተኛ የሀገሪቱን ሀብት የዘረፈ ሐውልት ከማሰራት ይልቅ፥ በብዙ ሽ የሚቆጠሩ የአካባቢ ረሀብተኞችን መመገብ ቅድሚያ ቢሰጠው አይሻልም ነበር ወይ ? ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠይቅም፡፡ ምክንያቱም ወያኔና ኣባ ገበረ መድህን-ጳውሎስ መጀመሪያውኑም ቢሆን በአፈጣጠራቸውም ይሁን በዓላማቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቆሙ ባለመሆናቸው ነው ፡፡ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጥ ሰው መነሻውና መድረሻው ለድሃና ለነደያን መቆም መሆኑ የሚያከራክር አይደለም ፡፡ ይህ ግን የወያኔን ሥርዓት የሚያራምዱ ግለሰቦች ዓላማና ተግባር ስላይደለ ኢትዮጵያ ሀገራችን አሁን ከወደቀችበት ሁኔታ በመገኘቷ ማንንም የሚያስደነግጥ፥ የሚያስገርምና የሚያሸብር ሊሆን አይችልም፡፡ ሀገራዊ መፍትሄ ከመፈለግ ግን ሊያዘናጋ አይገባውም ፡፡ መዘናጋት ከመጣ ብቻ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞት-ሞት የሚሞተው ! ያን ጊዜ ነው ወያኔና ተባበሪዎቹ የልብ ልብ የሚሰማቸው ፡፡ያን ጊዜ ነው ባዕዳን ደጋፊዎቻቸው፥ መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ በቁጥጥር ስር አስገብቷቸዋል ብለው ራሳቸውን ማታለል የሚጀምሩት ፡፡ ይህ እንደማይሆን ግን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልቡ ያምናል ፡፡ ምክንያቱም ባዕዳን ጠላቶቹንም ሆነ የወገን ደመኞቹን የመደምሰስ ኃይልና ኅብረት ስለሚኖረው ነው፡፡

ኢሕአፓ ዛሬ፥ የሀገራችን አካል ተቆረሰ፥ዳር ድንበሯ ተደፈረ፥የንፁሃን ደም ፈሰሰ፥ ታሪኳና ባኅሏ ረከሰ፥ ዜጋ ወደ ስደት ፈለሰ፥ ዕልፍ-አዕላፍ ልጆቿ በወህኒ ውስጥ ተሰቃዩ ፥ ለም መሬቷ ለባዕዳን ተቸበቸበ፥ ሀገራዊ ልዕልናዋ ተዋረደ፥ ተደፈረ፥ ወዘተ.. በማለት ብቻ አልተወሰነም፡፡ አይወሰንምም፡፡ መሆን የሚገባውን እያደረገ፥ የሚችለውን ሁሉ እያከናወነ የወቅቱን የኢትዮጵያ ሁኔታ ለመለወጥ የሚጠበቅበትን መሥዋዕት ለመክፈል ወደኋላ አይልም፡፡ ይህንን ሀቅ ደግሞ እንኳንስ ወገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ፥ ወያኔና ባዕዳን ደገፊዎቹ በሚገባ ያውቁታል ፡፡ ፓርቲው ሊጠፉላቸው ከቻለም ሊያጠፉት የተቻላቸውን ሁሉ እንደሚጥሩ እናውቃለን ፡፡ ከኢትዮጵያም ሕዝብ ይህ የተሰወረ አልሆነም ፡፡ አሳን

EthioLion

ለማጥፋት ከተፈለገ መጀመሪያ ባጎሩን ማድረቅ ነው ! እንደሚባለው ብሂል፥ መጀመሪያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማጥፋት ይሞክሩ እንደሁ እንጅ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨረሶ እስካልጠፋ ድረስ ግን ኢሕአፓ ሊጠፋላቸው አይችልም ። ይህ ደግሞ በታሪክ ሂደት ተሞክሮ ተሞክሮ ያልተሰካ ክስተት ነው ። ወያኔ ፥ ጨቋኝ ብሔር ብሎ የፈረጀውን ዜጋ ለማጥፋት ያደረገው እኩይ ተግባር እንዳልተሳካለት ሁሉ፥ " ፓርቲውንም ለመደምሰስ " ብሎ የሚያደርገው መፍጨርጨር ሳይሳካለት ቀርቷል። በመሆኑም እኛን የሚያስጨንቀንና የመያስጠብበን ሆኖ አላገኘነውም ። እንደማነኛውም ሁኔታና ሂደት ፥ ዛሬ የቅድሚያ አጀንዳችን ግን ያው የሀገራችን አሳሳቢ ሁኔታና የሕዝባችን ሰቆቃ ብቻ ነው ። በተለይም ከግንቦቱ የወያኔ ምርጫ በኋላ ያለውን የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ ስንመለከት ፥አያሌ ነገሮች አንፃራዊ በሆነ መልክ ተበውዘዋል ። ይህ ማለት ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ፥የምጣኔ ሀብት ፥ የማኅበራዊና የብሄራዊ ፀጥታ ሁኔታዎች ተለውጠዋል ማለት አይደለም ። እንዲያውም ከነበረው ሁኔታ በበለጠ መልኩ እየተባባሱ በመሄድ ላይ ናቸው ። ይህ ማለት ምን ማለት ነው ? በዘረኞች ሥርዓት ስር የወደቀችው ኢትዮጵያ የፖለቲካው ችግር ፥ የኢኮኖሚው ድቀት፥ የማኅበራዊው ቀውስ ፥የአስተዳደሩ ንቅዘት፥የፍትኅ-ርትዕ መጥፋት ፥ የሰብአዊ መብቶች መጣስ ፥ በጠቅላላው የዲሞክራሲ ጭላንጭል ደብዛው ጠፍቶ፥ የአንድ ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት ስር የሰደደበት ሁኔታ ተረጋግጧል ማለት ነው ። ይህ የአንድ አምባገነን ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት በማያሻማ መንገድ እንዲረጋገጥ የሆነው ደግሞ በወያኔው የግንቦቱ 2002 ምርጫ ለመሆኑ መላው ዓለም ታዝቧል። የኢትዮጵያም ሕዝብ ዓይኑ እያየ፥ጆሮው እየሰማ የወያኔን ውንብድና በድጋሜ ለመመዝገብ በቅቷል ።

በግንቦቱ የወያኔ ምርጫ የተከሰቱ ሁኔታዎች ቢኖሩ ፦

1ኛ. ለወያኔ የዲሞክራሲን ጭብል ለመስጠት ሽፋን ሲሰጡ የነበሩ ድርጅቶች ሁሉ በመለስ ዜናዊ ተንኮታኩተው በመቅረታቸው፥ የወያኔ ማንነት ይበልጥ መጋለጡ ፥

2ኛ. የዴሞክራሲያዊ ሂደት በኢትዮጵያ ተስፋው እየለመለመ ነው በማለት ሲያሽቃብጡ የነበሩ ባዕዳን የበላይ ጠባቂዎቹ ሀፍረታቸውን ለመደበቅ አለመቻላቸው፥

3ኛ. የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የባዕዳንንም ሆነ የወያኔን ፕሮፓጋንዳ ከንቱነት ይበልጥ ሊገነዘብ የቻለበትና ምንም ጊዜ ቢሆን ነፃነቱን እርሱ ብቻ ታግሎ እንደሚያስከብር በማያሻማ መልኩ ያረጋገጠበት ሁኔታ መፈጠሩና አማራጭ ለመፈለግ ዕድል ማግኘቱ፥

4ኛ. በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዐ-ምድር ለተቃዋሚ ኃይሎች አሰላለፍና አፈረጃጀት ዕይታ አዲስ ሁኔታ መፈጠሩ፥ ማን ምን እንደሆነ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በይበልጥ ሊታወቅ መቻሉ ፥

5ኛ. ከእንግዲህ ወዲህ ምን መደረግ አለበት? ለአዲሱ የትግል ምዕራፍ የኃይሎች አሰላለፍ ምን ሊሆን ይገባል? በዚህስ የትግል ጎራ እነማን ሊካተቱ ይገባል? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነተኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆናቸው ናቸው።

እነኝህን ከላይ የተጠቆሙትን ዐውደ-ሃሳቦች እንደ አሰፈላጊነቱ በአግባቡ እያገናዘቡ ለአዲሱ የትግል ምዕራፍ መሰናዶ ማድረግ ይዋል ይደር የሚባል ሊሆን አይችልም ። እራስን አዋርዶ ሀገርን እያዋረዱ መኖር ካልሆነ በስተቀር የተፈጠረውን አዲስ የትግል ምዕራፍ በመጠቀም ወያኔን አስወግዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ማብቃት ወያኔን እቃወማለሁ የሚለው ሁሉ የመጀመሪያው የትግል አጀንዳውና ግቡ ሊሆን ይገባል ። ከዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሀገራችን ትንሳኤ በኋላ የአምልኮ ጣዖት ሐውልት ፈርሶ፥ የጀግኖች ሰማዕታት አርበኞች ሐውልት እንደሚገነባ ልንጠራጠር አንችልም ።

!

EthioLion.com